## ክፍል 2 የግለሰብ ነፃነትን ማክበር

### ሀ. የንግግርና የኘሬስ ነፃነት

ምንም እንኳን ሕገ-መንግሥቱም ሆነ ያገሪቱ ህግ የንግግር የኘሬስ ነፃነትን ያጐናፀፉ ቢሆንም መንግሥት በተግባር እነዚህን መብቶች ገድቧቸዋል፡፡ መንግሥት ጋዜጠኞችን፣አሣታሚዎችንና አዘጋጆችን፥ የፈጠራ ያላቸውን መረጃዎች በማሳተማቸውና የፕሬስ ህጉን በመጣስ ወንጀል ሲከስና ሲያዋክብ ቆይቷል፡፡ መንግሥት ሁሉንም በሞገድ የሚተላለፉ ሚዲያዎች መቆጣጠሩን ቀጥሎ ነበር፡፡ የግልና የመንግሥት ጋዜጠኞች በተደጋጋሚ ራሳቸውን ሳንሱር ማድረግ ነበረባቸው፡፡

በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያሉ መገናኛ ብዙሀን ባብዛኛው የመንግሥትንና የገዢውን ፓርቲ የኢሕአዴግን አቋም የሚያንፀባርቁ ነበሩ፡፡ ይሁን እንጂ በቀጥታ የሚተላለፉ የሬዲዩና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች አንዳንዴ ቀጥታ የፓርላማ ክርክሮችንና የተቃዋሚ የፓርላማ አባላት አቋሞችን ልክ እንደ መንግስት ጋዜጦች ሁሉ ያቀርቡ ነበር፡፡ በመንግሥትና በግሉ ፕሬስ መሃከል የነበረው ግንኙነት ከምርጫው በኋላና በሰኔና ሕዳር 2005 ብጥብጦች ወቅት የበረውን ያህል የሻከረ ባይሆንም አብዛኛው በ2005 ይንቀሳቀሱ የነበሩት የግል ሚዲያዎች የጋዜጠኞችን እስርና መከሰስ ተከትሎ በመዘጋታቸው ወይም በራሳቸው ላይ ሳንሱር በማድረጋቸው ፀጥ እንዲሉ ተደርገዋል፡፡

በሜይ 2005 የተጀመሩት የመንግሥት እርምጃዎች ብዙዎቹን የግል ጋዜጦች ፀጥ አሰኝተዋል፡፡ ያገር ውስጥ ጋዜጠኞች በመንግሥት ተደጋጋሚ መዋከብ እንደሚደረስባቸው እንዲሁም አታሚዎች ጋዜጦቻቸውን እንዳያትሙ ጫና ይደረግባቸው እንደነበር ያማርራሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ከምርጫው በፊት እስከ አመቱ መጨረሻ የነበሩት የግል ጋዜጦች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ አሽቆልቁሏል፡፡ አሳታሚዎቻቸውና ዋና አዘጋጆቻቸው ከታሠሩ በኋላ ስምንት ጋዜጦች ታግደዋል፡፡ ስድስት ሌሎች ጋዜጦች ደግሞ በዚሁ የመንግሥት ርምጃ ምክንያት ወይም የመንግሥት ማተሚያ ቤቶች ጋዜጦቻቸውን አናትም ስላሉአቸው ሕትመት አቁመዋል፡፡ የተዘጉት ጋዜጦች ባንነድነት በሳምንት ወደ 400,000 ኮፒዎችን ያሠራጩ ነበር፡፡ ይህን የመንግሥት ርምጃ ተከትሎ ከቀሩት ስድስት የአማርኛ የፖለቲካ ጋዜጦች ባንድነት ወደ 40,000 ቅጂዎች ብቻ በስርጭት ላይ ነበሩ፡፡

አልፎ አልፎ የውጪ ጋዜጠኞች መንግሥትን የሚተቹ ፅሁፎችን የሚፅፉ ቢሆንም ዘገባቸውን እራሳቸው ሳንሱር እንዲያደርጉ በመንግሥት ጫና ይደርስባቸው ነበር፡፡ ባመቱ ውስጥ ጥቂት ዘጋቢዎች መንግሥትን የሚተቹ ፅሁፎች በማሳተማቸው ካገር ተባረዋል፡፡

ጃንዋሪ 21 ቀን የአሶሲየትድ ፕሬሱ ዘጋቢ አንቶኒ ሚቼል በአዲስ አበባ ውስጥ በተቃዋሚዎችና በፖሊስ መሃከል ደግሞ ስላገረሸው ግጭት በዘገበ ማግስት በ24 ሰዓታት ውስጥ ሃገሪቱን ለቆ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ የመንግሥት ንብረት የሆነው የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት (ኢዜአ) መንግስት ሚቼል እንዲባረር የወሰነው "የጋዜጠኝነት ስነ ምግባርን በመፃረር በተደጋጋሚ ጊዜ ያገሪቱን ምስል በማንቋሸሹ" እንዲሁም "ስለኢትዮጵያ ከእውነት የራቀ መረጃ በማሠራጨቱ" ነው ብሏል፡፡ የውጪ ዜጋ የነበረውና ለተባበሩት መንግሥታት ዜና አገልግሎት ለኢሪን የሰራው ሚቼል ባገሪቱ ከአምስት አመታት በላይ ሰርቶ ነበር፡፡

የፌብሯሪ 21 ቀን ደግሞ የውጪው ጋዜጠኛ የኢኒጐ ጊልሞር የጋዜጠኛነት ፈቃድ በማስታወቂያ ሚኒሲቴር ታግዷል፡፡ በታህሳስ 2005 "የኢትዮጵያው መሪ በሰብዓዊ መብት ምክንያት ተከሰሱ" በሚል ርዕስ ዘ ኦብዘርቨር

በተባለው የብሪታኒያ ጋዜጣ ላይ የዘገበው ዘገባ ከምርጫው በኋላ ተከሰቱ የተባሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ያካተተ ነበር፡፡

ጁን 23 የሳምንታዊውን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ጋዜጣ የ"ዘሳብ ሰሀራን ኢንፎርመር ሕትመት የቢሮ ለውጥ ማድረጉን አላሳወቀኝም በሚል የማስታወቂያ ሚኒስቴር አግዷል፡፡ ይሁን እንጂ ጋዜጣው ሁለቴም በፅሁፍ የቢሮ ለውጥ ማድረጉን ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አሳውቆ ነበር፡፡ በኦገስት 18 ሕትመቱን እንደገና እንዲቀጥል ፍቃድ አግኝቷል፡፡

በየካቲት 10 የመጀመሪያውን የሥርጭት ፈቃድ በመስጠት ሁለት የግል ሬዲዮ ጣቢያዎች ባገሪቱ ስራ እንዲጀምሩ ፈቅዷል፡፡ ባመቱ መጨረሻ ሁለቱም ሬዲዮ ጣቢያዎች ስራ አልጀመሩም ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኤጀንሲ ሁለቱን ጣቢያዎች፣ ዛሚ ፐብሊክ ኮኔክሽንንና ትንሳኤ ፋይን አርትስን፣ ከ12 ተፎካካሪዎች መሀል ባቀረቡት የገንዘብ አቅምና በፕሮግራሞቻቸው ይዘት እንደመረጣቸው አስታውቋል፡፡

በኦገስት ወር የደቡብ ክልላዊ መንግስት ስድስት የኤፍ ኤም ጣቢያዎችን በማቋቋም ስርጭት ለመጀመር ዕቅድ እንዳለው አስታወቀ፡፡ በዚያው ወር የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኤጀንሲ በደቡብ ክልላዊ መንግስት ወስጥ ለሚገኘው "ኮሪ" ለተሰኘው የማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያ ፈቃድ ሰጥቷል፡፡

ኦገስት 25 ቀን የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኤጀንሲ ከኢሕአዴግ ፓርቲ ጋር ግንኙነት ላለው ለራዲዮ ፋና የንግድ ፈቃደ ሰጠ፡፡ የኢትዮጵያ ሬዲዮም ለግል ቡድኖችና ግለሰቦች ለማስታወቂያና ሌሎች ፕሮግራሞች የአየር ጊዜ ሸጧል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የብዙሃን መገናኛ ኤጀንሲ የአምስት ሰዓት የኤፍ ኤም ሬድዮ ስርጭትና የ3 ሰዓት ያገር ውስጥ ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ስርጭት በቀን ሁለቴ ከዋና ከተማው ማድረጉን ቀጥሎ ነበር፡፡

ብቸኛውን የቴሌቪዥን ጣቢያ ሥራ● መንግሥት ያካሂድ የነበረ ሲሆን የዜና ስርጭቶችንም በጥብቅ ይቆጣጠር ነበር፡፡ የብሮድካስት ህጉ ግን ማንኛውም የፖለቲካም ሆነ የሃይማኖት ድርጅት የማሰራጫ ጣቢያ ባለቤት እንዳይሆን ያግዳል፡፡ ህጉ በተጨማሪም● የውጭ ዜጐችን ከባለቤትነት ያግዳል፡፡

ባመቱ የአለም አቀፍ ዜና ማሠራጫዎች ገደብ ነበረባቸው፡፡ የቪኦኤ ስርጭት ሆን ተብሎ እንዳይተላለፍ ይደረግ ነበር፡፡ መንግሥት ግለሰቦች የሳተላይት መቀበያ ዲሾች እንዲኖራቸው ፈቅዶ ነበር፡፡ ነገር ግን የዋጋው ውድነትና የኢትዮጵያ ቴሌኮሚዩኒኬሽንስ ኮርፖሬሽን ውሱን አቅም ይህንን ቴክኖሎጂ ባግባቡ መጠቀም እንዳይቻል አድርጓል፡፡

መንግሥት የጋዜጠኞችን እስር አግባብነት ለማሳየት ሃሰተኛ መረጃን በማሳተም፣ የብሔር ጥላቻን በመቀስቀስና በስም ማጥፋት ወንጀሎች ላይ ያሉ የህጉን አንቀጾች መጥቀሱን ቀጥሏል፡፡ ከተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ጋር 16 ጋዜጠኞች ባገር ክህደት፣ በዘር ማጥፋትና ሕገ-መንግሥቱን ለመናድ በመሞከር ወንጀል የተከሰሱ ሲሆን ወንጀለኛ ሆነው ከተገኙ እነዚህ ክሶች ከፍተኛውን የዕድሜ ልክ እስራት ወይም የሞት ፍርድ የሚያስፈርዱባቸው ናቸው፡፡

በኖቬምበር 2005 አምስት የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ጋዜጠኞች ከቅንጅቱ መሪዎች፣ ከሲቪል ማሕበረሰቡ አባላት፣ እንዲሁም ጋዜጠኞች ጋር ባገር ክህደትና ሕገ መንግሥቱን ለመናድ በመሞከር ወንጀሎች ተከሰው ነበር፡፡ ማርች 23 ቀን የውጭ መንግሥታትን ጫና ተከትሎ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ጋዜጠኞችና በሌሎች 13 ሰዎች ላይ የነበረውን የክህደትና የዘር ማጥፋት ወንጀሎች አንስቷል፡፡